# በሰሞኑ ወቅታዊ ክስተቶች ዙሪያ የቀረበ ትንተናዊ ዘገባ

*ለፀሐዬ ደባልቀው*

*ዋሺንግተን ዲሲ*
*የካቲት 22 ቀን 2010*

ሰሞኑን በዚህ በምንገኝበት በምድረ አሜሪካ የኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ጉዳይ በደጋፊዎች ጎራ የትኩረትና የውይይት ማዕከል ሆኖ ሲስተናገድ ሰንብቷል:: ደጋፊዎችና ሃገር ወዳዶች ከ35 ዓመት በፊት ተመሥርቶ የዛሬ 19 ዓመታት ከሌሎች አጋር የኢህአዴግ ድርጅቶች ጋር በመሆን የመንግሥትን መዘውር ይዞ ሃገራችን ኢትዮጵያ በዘለቄታው የሰላም፣ የልማት፣ የፍትህ፣ የዕኩልነትና የዲሞክራሲ መናሃሪያ ሆና ሕዝቦቿም የቡድንና የግለሰብ ነጻነታቸውን አስከብረው ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብታቸውን በአግባቡና ኃላፊነት በተመላበት ሁኔታ በመጠቀም ብሎም ይበልጥ በማዳበር ወደሚጓዙበት ብሩህ አቅጣጫ እያመራች ትቀጥል የድርሻውን በመወጣት ላይ ያለውን የሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ /ህወሓት/ የልደት በዓል በደማቅ ሁኔታ ሲያከብሩ ተስተውለዋል::

ይህ የሕወሓት የትጥቅ ትግል የተጀመረበትና ቀስ በቀስም በአሥራ ሰባቱ ፖለቲካዊ የትጥቅ ተጋድሎ መላውን የኢትዮጵያን ብሄር ብሄረሰቦችን ተሳትፎ በማካተት የአድሎአዊና የፍትህ አልባ ሥርዓቶችን መሠረት የናደው የሕዝባዊ እንቅስቃሴ ዕለት በመላው አሜሪካና ካናዳ መዋቅሩን በዘረጋው በሰሜን አሜሪካ የትግራይ ተወላጆች ማህበር /ማተስአ/ አስተባባሪነት ከየካቲት ወር መባቻ ጀምሮ የማህበሩ ደጋፊዎችና ሌሎች ኢትዮጵያዊያን በሚገኙባቸው ከተሞች በድምቀት መከበሩ ቀጥሏል::

በዚህ በአሜሪካ መናገሻ ከተማ በሆነችው በሃገሪቱ መዲና በዋሺንግተን ዲሲ ባለፈው ቅዳሜ የካቲት 20/2010 ላይ ወደ አንድ ሺህ የሚጠጉ የማህበሩ አባላትና ሌሎች ታዳሚ ኢትዮጵያዊያን በተገኙበት በደማቅ ሥነ ሥርዓት ተከብሯል::

በበዓሉ አከባበር ሥነ ሥርዓት የማተስአ የድጋፍ መግለጫ በንባብ ተሰምቷል:: በአካባቢያችን የሚገኙት የሕወሓት፣ የብአዴን ፣ የኦህዴድና የደቡብ ሕዝቦችና ብሔር ብሔረሰቦች ተወካዮች የዕለቱን ታላቅነትና በኢትዮጵያ ሕዝቦች ታሪክ ዘንድ የያዘውን አንጸባራቂ ምዕራፍና አገሪቱን ወደላቀ ሁለንተናዊ የልማት እርከን በማሸጋገር ሂደት ያስከተለውን ፋይዳ አስመልክቶ ገለፃ አድርገዋል:: ከዚህም በተጨማሪ የሶማሌ ሕዝቦች

ዲሞክራሲያዊ ድርጅትና የሃረሬ ሕዝቦች ዲሞክራሲያዊ ድርጅት ተወካዮች የእንኳን አደረሰንና የድጋፍ ቃል አሰምተዋል።

ከዚህም ሌላ ከሻዕቢያ መንግሥት ተቃዋሚ ኃይሎች መካከል የኤርትራ ዲሞክራሲያዊ ቃል ኪዳንና የኤርትራ ሃገራዊ አንድነት ዲሞክራሲያዊ ግንባር ተወካዮች በዓሉን አስመልክተው የሁለቱ ሕዝቦች የትግል ትስስርና ቀጣይ የወደፊት ግንኙነትን የሚፈነጥቅ የትግል አጋርነት መግለጫ አሰምተዋል። ይኸው በዋሺንግተን ዲሲ የተከበረው የሕወሓት ልደት በዓል በሃገርኛ ውዝዋዜና ባህላዊ ጭፈራዎች የታጀቡና በምሽቱም ያለፈውን መራራ ትግልና ውጤቱን የሚያመላክቱ መጣጥፎችና ግጥሞች በንባብ የቀረቡበት የሕወሓት ድርጅታዊ መግለጫና ሃገራችን በአሁኑ ጊዜ እያስመዘገበች የምትገኘውን ዘርፈ ብዙ ልማታዊ እመርታን የዳሰሱ በአሃዝ የተደገፉ የጽሑፍ መረጃዎችም ለግንዛቤ ቀርበው የትግሉንም ከ - እስከ የሚያመክላክቱ ዘገባዊ ፊልሞች በዲቪዲ ተቀነባብረው ቀርበዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለም የተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ም/ቤት በቅርቡ የኤርትራ መንግሥት በአፍሪቃ ቀንድ አካባቢ የሚያደርገውን ሕገ ወጥ ጣልቃ ገብነትን በማውገዝ የጅቡቲን ሉአላዊ ግዛት በሃይል ጥሶ መያዙን በመቃወም፣ በሶማሊያ ጽንፈኛ ውንና ሽብርተኛውን የአልሸባብ ቡድን በማስታጠቅና በማደራጀት የሚያደርገውን እኩይ ተግባር በመኮነን አጠቃላይ ማዕቀብ ጥሎበታል። ይኸንኑ በሚመለከት በዚህ በምንገኝበት ክፍለ አህጉር ውር ውር የሚሉት የኢትዮጵያ ተቃዋሚዎች ነን ባይ ጽንፈኞች ሰሞኑን ይዘውት የወጡት በይዘቱ ያው የከረመውን ድምፀት የሚያስተጋባ ግን በቅርፅ ተቆርቋሪና ለሃገር አሳቢ የሚመስል ካባን የደረበ የአዛኝ ቅቤ አንጓች ዓይነት አሰልቺ ጨኸታቸውን ሲያቀልጡት ተደምጧል።

ይኸውም በቅርቡ የተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ምክር ቤት በኤርትራ መንግሥት ላይ የጣለውን ማዕቀብ በተዛባ አደንቋሪ ውትወታ በማጀብ ተቃውሞአቸውን ማቅረባቸው ነበር።

እነዚህ ዓለም ያወቀውንና ፀሃይ የሞቀውን የሻዕቢያን መንግሥት ሽብርተኝነት፣ ፀጥታ አደፍራሽነት፣ የዕብሪትና የሰላም ማናጋት ጠረኛ ጣልቃ ገብ ፖሊሲን በመደገፍ የተሰለፉት በዚሁ በስደት ዓለም ሆነው የወያኔ መንግሥት ተቃዋሚዎች ነን ብለው በመሸ በጠባ ቁጥር የሚፏልሉትና የሚያቅራሩት ወገኖች ይዘውት ብቅ ያሉት በአዲስ

ፋሽን የተጀበነ አሮጌ ፈሊጥ፣ "የእምዮን ላብዬ እንዲሉ" ሻዕቢያ ላይ የተባበሩት መንግሥታት የጣለው ማዕቀብ የሻዕቢያ መንግሥት የፈፀማቸው ወንጀሎች ናቸው ተብለው የተጠቀሱትን ጥሰቶች እንዳሉ በመገልበጥ ለነዚህ ጉዳዮች መከናወንና ለተፈጠረውም ቀውስ በተጠያቂነት ወያኔን በሻዕቢያ ምትክ በመተካት ነው:: ይኸንንም በተቃውሞ ሰልፍ ለመደገፍ በዛሬው ዕለት February 22/2010 በተጠራውና በWhite House ዙሪያ በተካሄደው የተቃውሞ ሰልፍ ራሳቸው ተገኝተው ሌላም ኢትዮጵያዊ እነሱ በፈጠሩት መሰሪ የተረት ተረት ውንጀላ ተባባሪ እንዲሆን የሞከሩበት ዓይን ያወጣ ሸፍጥ ነው::

ይኸንኑ የጥቂት ኢትዮጵያዊያን ጽንፈኞች ሃገራዊ ክህደት ለማጋለጥ ሰሞኑን እነሱ የሚያካሂዱትን መሰሪ ቅስቀሳ በመመከት ብሎም በሃቀኛ ሃገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን ዘንድ ዕርቃኑን አስቀርቶ ደጋፊ አልባ ሆነው እንዲቀሩ ለማድረግ ሃገር ወዳዶች እግር በእግር እየተከተሉ መሳ ለመሳ እውነቱን ፍንትው አድርጎ በማስጨበጥ ትክክለኛውን ፈር የሚያስይዝ የሚዲያና የፕሮፓጋንዳ ሥራ ሲከውኑ ሰንብተዋል::

በዚሁ መሠረትም በሰላም፣ በሃገር ፍቅርና፣ በአንድ ኢትዮጵያ፣ በዘውድ ምክር ቤትና በመብት ሬድዮ ጣቢያዎች የኤርትራ መንግሥት ተቃዋሚዎችና በሃገራችን በመካሄድ ላይ ያለውን ሁለንተናዊ ለውጥ በሚገባ አሳማኝ በሆነ መንገድ የሚተነትኑ ሃገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን ቀርበው የፀጥታው ምክር ቤት በሻዕቢያ መንግሥት ላይ የጣለውን ማዕቀብ ትክክለኛነት፣ የሻዕቢያ መንግሥት ለከፍተኝነትና ተጠያቂነት የሚያሰርፁ ቃለ መጠይቆችን አድርገዋል:: በዚህ የሚዲያ ሥራ ሻዕቢያ ትኩረት ሰጥቶ እንዲደግፋት የሚማፀናቸው ኤርትራዊያን አሜሪካውያንና የጥገኝነት ጥቅማ ጥቅም የሚያገኙት ስደተኞች በዚህ ሰልፍ ላይ ከተገኙ ከሃገሪቱ ሕግ አንፃር የሚጠየቁበት አግባብ ስለመኖሩ ማስጠንቀቂያ አዘል ምክር የቀረበ ሲሆን በእሳት ከመጫወትና በአሁኑ ወቅት የአሜሪካን መንግሥት ተንተርሶ እያገኙ ያሉትን ከለላ እንዳያጡና የሻዕቢያ ሽርና ተንኮል ሰለባ እንዳይሆኑ ወገናዊ ምክር ተለግሶአቸዋል::

ከዚህም በተጨማሪ ከኤርትራ መንግሥት ተቃዋሚዎች ጋር የሚደረገው ሻዕቢያን የማጋለጥና ደጋፊ የማሳጣት ተግባር በጉዳዩ ዙርያ የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች አቋም የሚያንፀባርቅ በአያሌ የኢትዮጵያውያንና ኤርትራዊያን ድረ ገፆች ወጥቷል:: በዛሬው ዕለት የካቲት 22 ቀን 2010 ላይ፣ የተላለፈውን የማዕቀብ ውሳኔ እንዲነሳ በመጠየቅና ማዕቀቡ በኤርትራ ሕዝብ ላይ ያነጣጠረ ስለሆነ አግባብነት የለውም በሚል በሻዕቢያ አስተባባሪነት በWhite House ዙርያ በተካሄደው የተቃወም ሰላማዊ

ሰልፍ ላይ ከ12 የአሜሪካ ክልሎች እና፣ ከካናዳ የተሰባሰቡ በጥቂት መቶዎች የተቆጠሩ የሻዕቢያ ደጋፊዎች ተገኝተዋል:: የሻዕቢያ መንግሥት ተቃዋሚ አባላትም ማዕቀቡን በመደገፍ ባካባቢው የተገኙ ሲሆን ተቃዋሚዎችን ጠጋ ብለው ፎቶና ቪደዮ ሲያነሱ ውለዋል:: አንዳንድ ተቃዋሚዎችም የወያኔ ቅጥረኞች በማለት ሲጮሁባቸው የተደመጡ ሲሆን ፀጥታ አስከባሪዎች ግን ሁለቱም ወገኖች በሰላማዊ መንገድ ተቃውሞም ድጋፍም የማድረግ መብት እንዳላቸው አንዱ ሌላውን በኃይል ምርጫውን እንዳይከውን ለመከልከል ቢቃጣ በሕግ ቁጥጥር ሥር እንደሚውል በማስጠንቀቃቸው ሁለቱም ወገኖች ጉዳያቸውን በሰላማዊ መንገድ አቅርበዋል:: ይህ በእንዲህ እንዳለም ሰሞኑን የኢትዮጵያ መንግሥት ተቃዋሚ ነን የሚሉ አንዳንድ ጅብደኞች ኢትዮጵያውያን ከሻዕቢያ ደጋፊዎች ጎን እንዲሰለፉ ውትወታ ቢያደርጉም ኢትዮጵያውያን ለዚህ የተንጋደደ ጥሪ ምላሽ እንዳልሰጡና ሦስት ሰዎች ብቻ የሻዕቢያን ደጋፊዎች ሰልፍ መቀላቀላቸው ለማወቅ ተችሏል::

ሰላማዊ ሰልፉ ከመካሄዱ በፊት አንድ ቀን ደቀም ብሎ በዋሺነግተን የኤርትራ ኤምባሲ ሰልፈኞች የአሜሪካንን መንግሥት የሚያወግዙ መፈክሮች ይዘው ለመውጣት እንደማይፈልጉና ተጠያቂ ለመሆን አለመዘጋጀታቸውን በማጤን በዛሬው ዕለት ሰልፍ በወጡት ተነግበው ከነበሩት መፈክሮች መካከል አንድም ፀረ-አሜሪካ አባባል እንዳላስተናገዱ ለማወቅ ተችሏል::